በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል አሥራ ሁለት


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ነሐሴ ፲፰ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- የቤተ ክርስቲያን ታላቁ ሚና ጸሎት ነው፡፡ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግኑኝነት ያጸናል፡፡
- ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ‹‹ጸሎት በመላ ሕይወታችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግኑኝነታችንን የምናጸናበትና ሕይወትንም ያለማቋረጥ የምንጸልይባት አንድ የጸሎት ጎዳና የምናደርግባት መሣሪያ ናት፡፡›› ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ‹‹ወደ እግዚአብሔር የማይጸልይ ሰው ነፍሱ የተለየችው - በመንፈሱ የሞተ ሙት ሰው ነው፡፡ ጸሎት ታላቅ መሳሪያ፣ መጨረሻ የሌላት ሀብት፣ ፈጽመን እንዳንወድቅ የምታደርገን ባለጠግነት፣ የጸጥታ ወደብና መሸነፍ የማያገኞት ጸጥታ ናት፡፡›› በማለት ተናግረዋል፡፡
- ጠላትን የምናሸንፍባት የእግዚአብሔር ኃይል የምትገኘው በጸሎት ነው፡፡ በአስጨናቂው ዓለም ውስጥ በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር እንድንሆን አቅፋ የምትይዝ መሸሸጊያች ጸሎት ናት፡፡
- በዚህም የተነሳ በየግላችን ከምናደርገው ጸሎት በተጨማሪ የቤተሰቡ አባላት በአንድነት ሆነው ሊጸልዩ ይገባል የምንለው ከላይ የተገለጸው ክብካቤ ከእግዚአብሔር እንዲደረግላቸው ነው፡፡
- በቤተሰብ ሆኖ የመጸለይን አስፈላጊነት የምናስተምርበት ምክንያት፡-
    - አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና፡፡» *ማቴ 18፡20፡፡* በማለት እንደተናገረው እግዚአብሔር በቤተሰባዊ ሕይወታችን ስለሚገኝ

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- በግላቸው ከመጸለይ የሚሰንፉና ቸልተኞች የሆኑ የቤተሰቡ አባላትን እንዲጸልዩ ስለሚያበረታታ
- በቤተሰብ ጸሎት አባላቱ ከልብ ሆነው የሚጸልዩት ጸሎት በዚያ ያሉትን ልብ ወደ በጎ ስለሚመልስና ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስላለው
- የቤተሰብ ጸሎት ቤተሰቡን በእግዚአብሔር ስለሚያዋሕዳቸው
- ልጆች በቤተሰብ ጸሎት መጸለይንም ሆነ፣ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው፣ እግዚአብሔርን እንዴት ሊያከብሩት እንደሚገባና በፊቱም እንዴት በፍርሐት መቆም እንዳለባቸው የሚማሩበት ት/ቤት ስለሆነ ነው፡፡

- ታዲያ ዋናው ጥያቄ በቤተሰብ የጸሎት ጊዜ ምን እንጸልይ? የሚል ነው፡፡

1. <u>የዘወትር ጸሎት፣ ውዳሴ ማርያምን፣ መዝሙረ ዳዊትንና ሌሎችንም</u>

- እነዚህ ጸሎቶች የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ <u>*ማቴ 6፡9-13፣ ሉቃ 1፡26-58፣ኢሳ 6፡1-7*</u>
- ‹‹እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥ መተርጐም አለው፤ ሁሉ ለማነጽ ይሁን፡፡›› <u>*ቀዳ ቆሮ 14፡26፡፡*</u> ፣ ‹‹በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፡፡›› <u>*ኤፌ 5፡19፡፡*</u> እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፡፡
- የዳዊት መዝሙር ‹‹ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም፡፡›› <u>*ያዕ 4፡3*</u>፣ ‹‹እጃችሁንም ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፥ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል፡፡›› <u>*ኢሳ 1፡15*</u> እንዳሉት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተዘመረ መዝሙር ነው፡፡ እኛም ልቦናው በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሞላ መዝሙሩን እንጸልያለን፡፡

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- እኛ በየግላችን በእግዚአብሔር ፊት ተግተን ለመቆም የሚያስችለን የተሰበሰበ ሐሳብና የተጠኑ ቃላቶች (ዐረፍተ ነገሮች…) የሌለን ቢሆንም በዘወትር ጸሎት (አአትብ ገጽየ፣ ነአኵተከ፣ አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ገብርኤል፣ ጸሎተ ሃይማኖት፣ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ፣ እሰግድ፣ ስብሐት፣ ሰላም ለኪ)፣ ውዳሴ ማርያም፣ መዝሙረ ዳዊትና ሌሎችም በቅዱሳን የተጸለዩ ጥልቅ መንፈሳዊ መልእክት የያዙ ጸሎታችንንም የሚያጠነክሩ ጸሎት ሊይዘው የሚገባውን ፍሬ ነገር ምስጋናን፣ ውዳሴን፣ ልመናን እንዲሁም የምናምነውንና የምንመሰክርበትን ትምህርት ያካተቱ ናቸው፡፡
- በዚህ ጸሎት ልመናችን እንደተፈጸመልን እየገለጽን ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገራለን፡፡
- ‹‹አቤቱ፥ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ! በኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው፡፡›› እንዳልን ሁሉ ‹‹በቃሌ ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ ከተቀደሰ ተራራውም ይሰማኛል፡፡›› ብለን እንጸልያለን፡፡ *መዝ 3፡፡*
- ‹‹አቤቱ፥ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፥ በመዓትህም አትገሥጸኝ፡፡›› እንዳልን ሁሉ ‹‹ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ፥ ከእኔ ራቁ፥ እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና፡፡›› ብለን እንጸልያለን፡፡ *መዝ 6፡፡*
- ‹‹አቤቱ፥ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ?፡፡›› እንዳልን ሁሉ ‹‹እኔ ግን በቸርነትህ ታመንሁ፥ ልቤም በመድኃኒትህ ደስ ይለዋል፡፡የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፥ ለልዑል እግዚአብሔር ስምም እዘምራለሁ፡፡፡፡›› ብለን እንጸልያለን፡፡ *መዝ 13፡፡*
- በዚህም የተነሳ በጸሎታችን ፍጻሜ ሰላምን የተሞላን እንሆናለን፡፡ በቀን ሰባቱን ሰዓታት ጠብቀው የሚጸልዩም መላውን ቀን እግዚአብሔርን ሲገናኙት ይውላሉ፡፡ *መዝ 118፡164፡፡*
- በጸሎት ውስጥ ትምህርት ስለሚገኝ በቤታችንም ልንጸልይ ይገባናል፡፡ ‹‹ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፡፡›› *መዝ 1፡1፡፡*

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- ማር ይስሐቅ ‹‹የመዝሙረ ዳዊትን ጸሎትና የአገልግሎትህንም ፍሬ ጣዕም በመንፈስ ቅዱስ ለማጣጣምና ደስ ለመሰኘት የምትወድ ከሆነ ስንት መዝሙራትን እንደደገምህ ሳይሆን ለምትጸልየው ጸሎት ትኩረት በመስጠትና የምትጸልየውንም በመረዳት ጸልይ፤ በዚህም እግዚአብሔርን እየተነጋገርህና እያመሰገንኸው እንደሆነ በእውነት ትገነዘባለህ፡፡›› እንዳለ እያደረግን እንጸልይ፡፡

2. <u>በጸሎት ጊዜ ከቤተሰቡ አባላት የሚጠበቁ ነገሮች</u>

- በቤታችን ለምንጸልየውም ጸሎት ትኩረት ሊኖረን ይገባል፡፡ ይህም የግል ጸሎት የሚከተሉት መገለጫዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

***እግዚአብሔርን በመፍራት መጸለይ***

- ከእግዚአብሔር ጋር ስንነጋገር እንደ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በፊቱ ወድቀን በመስገድ ሊሆን ይገባል፡፡ «ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፡፡ ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ፡፡» *<u>ራእ 4፡10-11፡፡</u>* «መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡፡» *<u>ራእ 7፡11፡፡</u>* እንደተባለ፡፡

***እንደ እግዚአብሔር ልጆች በመሆን መጸለይ***

- እግዚአብሔር «አባታችን ሆይ …» ብላችሁ ጸልዩ በማለት እንዲሁም በሞቱም ወደ ክብራችን መልሶ ልጆቹ እንዳደረገን በመገንዘብ እንደ ልጆች ሆነን መጸለይ ይገባናል፡፡

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

2. **በጸሎት ጊዜ ከቤተሰቡ አባላት የሚጠበቁ ነገሮች…**

***በእምነትና በተስፋ መጸለይ***

- እምነት እግዚአብሔር በማይወሰን ፍቅሩና ኃይሉ እንደማይተወንና እንደሚጠብቀን ‹‹ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡›› እንደተባለው ተቀብሎ መኖር ነው፡፡ *ዮሐ 1፡3፡፡*
- በዚህም እምነታችንና ተስፋችን እግዚአብሔር በጊዜው ምላሹን እንደሚሰጠን እንታመናለን፡፡

***ራስን በመስጠት መጸለይ***

- *ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ይሁን እያልን እንደምንጸልይ ፈቃድህ ይሁን ብለን ሁሉን ለእግዚአብሔር አሳልፈን በመስጠት መጸለይ ይኖርብናል፡፡*
- *ይህም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ‹‹የወይን ጠጅ የላቸውም፡፡›› ዮሐ 2፡3፡፡* በማለት ችግራቸውን በጌታችን ፊት እንዳቀረበችላቸው እና በእምነት (በአማላጅነትዋ) የቀረበ ጸሎትም እንደሚፈጸም በማመን ‹‹*የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ›› ዮሐ 2፡5፡፡* እንደ አለቻቸው ሆኖ መጸለይ ማለት ነው፡፡ ጌታችንም ጊዜው ባይደርስም ውሃውን ወደ ወይን በመለወጥ ለእመቤታችን ለልመናዋ መልስ ሰጠ፡፡ ስለዚህ እመቤታችን ለቅዱስ ገብርኤል ‹‹እንደ ፈቃድህ ይሁንልኝ ይደረግልኝ፡፡›› *ሉቃ 1፡38* ያለችውን ከማለት በቀር የኛን ፈቃድ በእግዚአብሔር ላይ ለመጫን ከመሞከር እንጠንቀቅ፡፡
- የምንጸልየውም ጸሎት ልጆቻችን ሊረዱት የሚችሉት የልጆችንም የአዋቂዎቹንም ፍላጎት ያቀፈ ይሆን ዘንድ በቀላል ቋንቋ የሚቀርብ ሁሉም ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገሩ መሆኑን በሚረዱበት መንገድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህም እንደ ቤተክርስቲያናችን ጸሎት በምስጋና የሚጀመር ሊሆን ይገባዋል፡፡ *ፊሊ 3፡10፡፡*
- በጸሎታችን የእግዚአብሔርን ጽድቅና መንግሥት ፣ ኃጢአታችንም ይሰረይልን ዘንድ መጠየቅ ይገባናል፡፡ ‹‹አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡›› *መዝ 50፡10፡፡*

# <u>ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን</u>

2. **በጸሎት ጊዜ ከቤተሰቡ አባላት የሚጠበቁ ነገሮች…**

***በፍቅር መጸለይ***

- ከልቡ የሚጸልይ ሰው ስለራሱ ብቻ ሳይሆን ስለሌሎችም ይጸልያል፡፡ ‹‹ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፥ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ፡፡›› *<u>ዕብ 13፡3፡፡</u>*
- ነቢዩ ሳሙኤል እንደተናገረው ለሌሎች አለመጸለይ ኃጢአት ነው፡፡ ‹‹ደግሞ መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ፡፡›› *<u>ቀዳ ሳሙ 12፡23፡፡</u>*
- ልጆቻችን ለቤተ ክርስቲያን ሰላም፣ ለፓትርያርኩ፣ ለሊቃነ ጳጳሳት፣ ለኤጲስ ቆጶሳት፣ ለቀሳውስት፣ በሰንበት ት/ቤት ለሚያስተምሯቸው መምህራን፣ ለአገራቸው፣ ለመሪዎች፣ በተለያየ መንገድ ለሚያገለግሉአቸው ሁሉ እንዲጸልዩ እናስተምራቸው፡፡ ጌታችን ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና፡፡›› *<u>ማቴ 5፡44፡፡</u>* በማለት እንዳስተማረን፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ ለሚወግሩት ‹‹ተንበርክኮም፡፡ ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡ ይህንም ብሎ አንቀላፋ፡፡›› *<u>የሐዋ 7፡60</u>* እንደተባለ፣ ጌታችንም ‹‹አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው፡፡›› *<u>ሉቃ 23፡34፡፡</u>* ብሎ እንደነገረን ለጠላቶቻችንም እንጸልይ፡፡

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

2. **በጸሎት ጊዜ ከቤተሰቡ አባላት የሚጠበቁ ነገሮች…**

***በቤተ ክርስቲያን ዜማዎች በመጠቀም መጸለይ***

- በጸሎታችን ጊዜ የቤተክርስቲያንን ዜማ የተከተሉትን ምስጋናዎች እንጠቀም፡፡ ይህን ካደረግን የቤተ ክርስቲያን ዜማዎች ለጆሮአችን እንግዳ አይሆኑም፡፡
- የተወደዳችሁ ምዕመናን በቤታችሁ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ወዴት አለች? ቤተሰቡንስ በአንድነት የሚያሰባስበውስ የቤተሰብ ጸሎት ወዴ አለ?

***የቤተሰብ ጸሎት የሚደረግበት ቦታና ጊዜ***

- ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግኑኝነት በጸሎት የጠበቀ መሆኑ ‹‹እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፡፡ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም፡፡›› *ማቴ 5፡14፡፡* እንደተባልን ለሌሎች ብርሃን፣ መንፈሳዊ በረከት እንዲያገኙም ምክንያት ለመሆን ያበቃናል፡፡

***ቦታ***

- ጌታችን ከተጠመቀ በኂላ 40 ቀንና ሌሊት ለመጾም ወደ ገዳም እንደሄደ፣ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ያደርግ እንደነበረው በመኖሪያ ቤታችን ለዚሁ የተዘጋጀ ልዩ ክፍል (ሥፍራ) እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡
- እንደዚህ ስንጸልይ ልቦናችን ወደ ሰማያዊ አገር ይወሰዳል፣ በደብረ ታቦርም እንደሆንን ይሰማናል፡፡
- አእምሮአችንም ተለውጦ በመንፈሳዊ ዓይን ከምድር ወደ ሰማይ በተዘረጋ መሰላል በመላእክቱ አማካይነት ጸሎታችን ሲያርግ ሰማያዊውንም በረከት መለኮታዊውንም ስጦታ ሲያወርዱልን እናያለን፡፡ እንደ አባታችን ያዕቆብም ‹‹ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው፡፡›› ማለት ይቻለናል፡፡ ***ዘፍጥ 28፡15፡፡***

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

*ቦታ…*

- በምንጸልይበት ቦታ እንደ ሙሴ ልቦናችንና መላ ሕይወታችን በሰማያዊው መገለጥ ደስ ተሰኝቶ ታላቁን ስጦታ እንድንቀበል ያስችለናል፡፡
- በምንጸልይበት ሥፍራ ሆነን ጌታችን እናየዋለን፡፡ ነገር ግን ስለ እኛ እያለቀሰ ሳይሆን ‹‹ለአንተ ኃይልና ክብር ለዘላለም ይሁን፡፡›› እያልን በፊቱ እየተንቀጠቀጥን፣ በደስታና በሐሴት እናየዋለን፡፡
- ቀኑን ሁሉ ካሳለፍነው የዓለም መከራ በኋላ ጌታችን በጎልጎታ እንደተደረገበት ሆነን በፊቱ ለጸሎት መቆማችን ከሕማሙ የምንካፈል ሆነን እንደታዛቢ ሳይሆን ከእርሱ ጋራ ሰቅለን እንድንገኝ ያደርገናል፡፡
- በማለዳ ተነስተንም ስንጸልይ የጌታችን ትንሣኤ ምስክሮች ሆነን ከእርሱ ጋር ጠላታችን ዲያቢሎስን አሸንፈን ቀኑን (ዕለቱን) በታላቅ ድል አድራጊነት እንጀምራለን፡፡
- ወደ ጸሎት ቦታችን ስንገባ ወደ ደብረ ዘይት ሲያርግ ልናየው ሳይሆን ወደ ሰማያዊው አገሩ ሊያስከትለን እንደሄድን ሆነን ሰማያዊ አክሊል እየታየን ሰማያውያኑ ካህናት በዙፋኑ ለተቀመጠው ንጉሥ እየሰገዱ እንገባለን፡፡
- በጸሎት ሥፍራችን በገነት ያሉ ቅዱሳንና መላእክቱ ጸሎታችንን የከበቡት ሆኖ ይሰማናል፡፡ ስለዚህም በቤታችን የተለየ የጸሎት ሥፍራ ሊኖረን ያስፈልገናል፡፡ በቦታውም የሥላሴ፣ የልደቱ፣ የደብረ ታቦር፣ የትንሣኤው፣ እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል የሚጠቀምባቸው አማላጆቻችን የሆኑ የእመቤታችን፣ የቅዱሳን መላእክት፣ የቅዱሳን ሰዎች፣ የመስቀል… ሥዕል እንዲኖረን ያስፈልገናል፡፡
- ይህም የጸሎት ሥፍራ ጸጥታ የሰፈነበት ሊሆን ይገባዋል፡፡

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

*የጸሎት ጊዜ*

- *መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፡፡›› ሉቃ 18፡1፣ ‹‹ሳታቋርጡ ጸልዩ፡፡›› ቀዳ ተሰ 5፡17፡፡* በማለት እንደነገረን ቤተሰቡ ለሁሉም በሚስማማ መልኩ ከሰባቱ የጸሎት ጊዜያት (የነግህና የሠርኩ በቤተ ክርስቲያን ሆኖ) ቢያንስ ሁለት ጊዜ ሊጸልዩ ይገባል፡፡
- ከምንጸልያቸው ጸሎቶች ጋር *‹‹እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፡፡ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው፡፡በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ፡፡በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው፡፡›› ዘዳግ 6፡6-9* እንደተነገረን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይገባናል፡፡ *ሕዝ 3፡17፡፡*
- ልጆች ከመኝታቸው በፊት በቀኑ መጨረሻ የእግዚአብሔርን ቃል (ትእዛዝ) መስማታቸው ከሁሉ የበለጠ ያስደስታቸዋል፡፡
- *‹‹የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ከደም አድነኝ፡፡›› መዝ 50፡14፡፡* ብለን የምንጸልየው እግዚአብሔር ለልጆቻችን መንፋሳዊነት ክብካቤ ባለማድረጋችን ከመጠየቅ እንዲታደገን ነው፡፡
- *ወላጆች ሆይ ምን ዓይነት መጻሕፍት ታነባላችሁ? በቤታችሁስ ያለ መጽሐፍ እንዴት ያለ ነው? የልብ ወለድ፣ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ መጻሕፍት ናቸው? ጋዜጦችና መጽሔቶች ናቸው? እነዚህን ማንበብ ጥፋት ባይሆንም ለመንፈሳውያን መጻሕፍት ጊዜ ነፍገን የምናደርገው ከሆነ ጥፋት ነው፡፡*
- *መጽሐፍ ቅዱስና መንፈሳውያን መጻሕፍትን ማንበብ በዚህም በወዲያኛውም ዓለም ጥቅም አለው፡፡*

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- ስለዚህ እንደ ደቀመዛሙርቱ ነፍሳችንን ከአምላካችን እግር ሥር አድርገን ቃሉን በማንበብ እንጥቀማት፡፡
  - መንፈሳውያን መጻሕፍትን የምናነበው ልጆቻችንን ማስተማር እንድንችል ነው፣
  - እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ በመኖር ለልጆቻችን ምሳሌ እንድንሆናቸው ነው፣
  - ልጆቻችን እኛን ተከትለው እንዲያነብቡ ነው፡፡
- ስለዚህ ስናነብ ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ሰጥተን በቤተሰብ ሆነን የምናነብበት ክፍለ ጊዜ ይኑረን፡፡
  - ቤተሰቡ በጋራ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብበት ክፍለ ጊዜና ቦታ ይኑረው፡፡
  - አባት ከቤተ ሰቡ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት እንዲችል ለብቻው የሚያብበት ክፍለ ጊዜ ይኑረው፡፡
  - ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ከማንበብ በፊት መጸለይን እንዳስተማረችን ከማንበባችን በፊት እንጸልይ፡፡
  - እግዚአብሔር የመጻሕፍቱን የትርጉም ደጆች ይከፍትልን ዘንድ አንብበን ስንፈጽምም እንጸልይ፡፡ ‹‹ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ፡፡›› *መዝ 118፡18*፣ ‹‹መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡›› *ቀዳ ቆሮ 2፡10*፣ ‹‹እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ፥ እንደ ቀድሞውም፡፡ ሳሙኤል ሳሙኤል ብሎ ጠራው፡፡ ሳሙኤልም፡፡ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለው፡፡›› *ቀዳ ሳሙ 3፡10፣ ማቴ 11፡25፣ ያዕ 1፡21…*

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- በምናነብበት ጊዜ ትርጉሙን ያልተረዳነው አንዳች ነገር ቢኖር የቤተ ክርስቲያን አባቶችን እንጠይቅ፡፡
- ስለዚህም ለማስታወስ ወንጌል ሲነበብ ‹‹እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ፥ ልጅ አባቱን፥ ባሪያም ጌታውን ያከብራል እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ ወዴት አለ? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦ እናንተም፡፡ ስምህን ያቃለልን በምንድር ነው? ብላችኋል፡፡›› *ሚል 1፡6፡፡* እንደተባልን ቆመን እንድንሰማ ዲያቆኑ ያሳስበናል፡፡
- የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽመን እናክብረው እንጂ ታመን ካልሆነ ተኝተን፣ እየበላን ወይም በሌሎች ነገሮች ተይዘን ከማንበብ እንቆጠብ፡፡
- ለልጆች ሥዕላት ያሉት መጽሐፍ ቅዱስ ኖሮን እንዲያነቡ እያበረታታን እንዲያነቡ ብናደርጋቸው ኃላፊነት ይሰማቸዋል የማንበብም ፍቅር ያድርባቸዋል፡፡
- ‹‹ምርኮኛ ፈጥኖ ይፈታል አይሞትም ወደ ጕድጓድም አይወርድም፥ እንጀራም አይጐድልበትም፡፡›› *ኢሳ 51፡4፡፡* እንደተባለ ሲነበብልን በጥሙና መስማት ይገባናል፡፡
- ከተነበበልንም የቤተሰቡ አባላት የዕለቱን ጥቅሳቸውን እንዲመርጡ፣ ሕፃናትም ጥቅሱን በወረቀት ጽፈው የሚታይ ቦታ እንዲለጥፉት ቢደረግ ሁሉም ቃሉን ሊያስታውሰው ይችላል፡፡ *ዘዳግ 6፡8፡፡*
- ጥቅሱም ቀኑን ሙሉ ሊታወስና እያንዳንዳቸውም ጥቅሱን እንዴት በሕይወታቸው እንዴት ተግባራዊ እንዳደረጉት መማከር ይገባል፡፡
- ለብ ያልን ሆነን እንዳንቀር ምንም ይሁን ምን የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ ማናበብ ይገባናል፡፡ *ራእ 3፡15-16፡፡*

# ጸሎት በቤታችን ባለች ቤተ ክርስቲያን

- የሳምንቱ መጨረሻ በሳምንቱ የተነበቡልንን የምንከልስበት፣ ያስታወሱትንም ለማበረታታት የምንሸልምበት መንገድ ሊኖረን ይገባል፡፡
- በዓመታዊ በዓላትም ዕለት እንደ በዓሉ ታሪክ፣ የምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጥቅሶችም እንዲጠኑ ማድረግም ተገቢ ነው፡፡
- ልጆች በቤተ ክርስቲያን በሚደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የጥያቄ ውድድሮች እንዲሳተፉ ብናደርጋቸውም ተገቢ ነው፡፡
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! ቤተ ክርስቲያንን በቤታችሁ ልታዩአት የምትሹ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስን (መንፈሳውያን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን) እናንብብ፡፡
- ለመንጋው ሁሉ በጎ ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ቤተ ክርስቲያንን አስቀድመን በአገልጋዮቹ ቤት ማየት ይገባናል፡፡ ሁሉን እንድንፈጽም በጎ ምሳሌም እንድንሆን አምላካችን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን፡፡ ቅዱሳን በአማላጅነት አይለዩን አሜን፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org